# 121ኛው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል በዳላስ ቴክሳስ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

የመላው ጥቁር ኩራት የሆነውን የአድዋ ድል 121ኛውን መታሰቢያ በዓል በርካታ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት በዳላስ ቴክሳስ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል። የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓሉን ያዘጋጀው በዳላስና ፎርትወርዝ የኢትዮጵያውያን ጉዳዮች የውይይት መድረክ ሲሆን ዘንድሮ ሲያዘጋጅ ለሦስተኛ ጊዜ ነው።

ስብሰባው በዳላስ ቴክሳስ የሰዓት አቆጣጠር 4 ሰዓት የተጀመረ ሲሆን ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ኢትዮጵያዊነት ወኔ የተሞላበትና ድል ድል የሚሸት ነበር። የዝግጅቱ መድረክ መሪ አቶ መንግስቱ ሙሴ ስብሰባውን በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ኮልፌ ቀራንዮ በተለምዶ ቆሼ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በወገኖቻችን ላይ በደረሰው እልቂት ህይወታቸው ያጡትንና የተጎዱትን እንዲሁም አጥንታቸው ከስክሰውና ደማቸውን አፍሰው ለአድዋ ድል ላበቁን ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችንን በማሰብ አስጀምረውታል። በመቀጠልም በዓሉ አዘጋጅ የሆነውን በዳላስና ፎርትወርዝ የኢትዮጵያውያን ጉዳዮች የውይይት መድረክ ሰብሰቢ አቶ ኃይሌ በመጋበዝ የእንኳን አደረሳችሁና እንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት አስተላልፈው የማህበሩን ተግባራት አብራርተዋል።

በዳላስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የጋራ መረዳጃ ማህበር የቦርድ ተወካይ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ቦርዱን ወክለው ንግግር ያደረጉ ሲሆን ይህን ትልቅ በዓል ያዘጋጀውን የውይይት መድረክ አመስግነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትኩረት እየተሰጠው መምጣቱ እንዳስደሰታቸው ገልፀዋል። በመቀጠልም ወ/ሮ ራሔልና ልጆቿ(ናሆምና መቅደስ) "የአድዋ ድል" የተሰኘ ግጥም አቅርበዋል።

በዝግጅቱ መካከል ላይ ተጨማሪ ንግግሮችና ድል ድል የሚሸቱ አገራዊ ዘፈኖች የቀረቡ ሲሆን የዝግጅቱ እንግዳ ሆነው የተጋበዙት ዶ/ር ማስፍን ገናናውና ፕ/ር ኃይሌ ላሬቦ የአድዋ ድል የተመለከተ ሰፊ የሆነ ትምህርታዊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ሁለቱም የዝግጅቱ እንግዶች ያደረጉትን ንግግር ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ትምህርት ሰጪ በመሆናቸው በቅርቡ ለሁሉም እንዲደርስ እናደርጋለን።

ሌላው የፕ/ር ኃይሌ ላሬቦ ባለቤት ወ/ሮ እስከዳር ባለቤታቸው ለአገራቸዉ ያላቸውን ፍቅር፣ የሚያደርጉት ትግል አድንቀው፤ ለቤታቸውም ፍቅር የሆኑ ጥሩ አባወራ መሆናቸውን ገልፀዋል። በቅርቡ በኢሳትና ዶቼቤላ ሬድዮ ጣቢያ በሰጡት ቃለመጠይቅ ያልተደሰቱ ግለሰቦችና ቡድኖች ግን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በጎደለው መልኩ በቤተሰቦቻቸው ላይ ከፍተኛ ዛቻ ከማቅረባቸውም በላይ ባለቤታቸው ከስራ እንዲባረሩ ለማድረግ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደነበር ያስረዱ ሲሆን ፕ/ር ኃይሌ ላሬቦ ላይ የሚደርሰው በደም የኛም በደል ነው በማለት ከጎናቸው ለቆሙት ሁሉም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በመጨረሻም ዝግጅቱን በተመለከተ የተዘጋጀውን ኬክ የእለቱ እንግዶች በአንድ ላይ ቆርሰው የፕሮግራሙ ፍፃሜ ሆኗል።





